# መልካም አስተዳደር በማስፈን ሂደት-ተግዳሮቶችና ተስፋዎች

ያሬድ -ከመቐለ (የህዝብ ግኑኝነት ቢሮ)

በትግራይ ክልል ከተለዩ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች መካከል በዋናነት በግብር፣ በበጀት አስተዳደር፣ በመሬትና ፍትህ አገልግሎት የሚታዩ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች፤ በሲቪል ሰርቫንት ያለው የአገልጋያነት ዳተኝነት፤ ህዝብን በመስማት ፈጠነ ምላሽ በመሰጠት ረገድ የታዩ ጉድለቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ ችግሮች ለመፍታት በዋናነት ክልሉ ቀደም ብሎ የሲቪል ሰርቪስ፣ የከፍተኛ ፍርድቤት ፕሬዝደንት፣ የህዝብ ምክርቤት አፈ ጉባኤ፣ የአሰተዳደርና ፀጥታ፣ የከተማ ልማት ንግድና ኢንዳስትሪ፣ የገጠር መሬት አስተዳደር፣የገቢዎች ባለስልጠን፣ የህዝብ ቅሬታ ሰሚ ሴክተሮች የያዘ አደረጃጀቶች እንዲሁም በዚህ አመት የህዝብ ግኑኙነት መዋቅር ያካተተ የመልካም አስተዳደር ግንባር ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ተቋቁሞ የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ ትርጉም ወደ ሌለው ደረጃ ለማውረድ በጋራ እየገመገመ፣ አሰራሮች እያወጣ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። የመሪ ድርጅትና የመንግስት ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ በመጀመሪያው የማጥራት ስራ ከተወሰዱት እርምጃዎች በተጨማሪ እሰከ ቀበሌ ድረስ የዘለቀ የለማትና መልካም አስተዳደር ህዝባዊ ኮንፈረንሶች መሰረት በማድረግ በየደረጃው ያለው አመራር መልሶ ራሱን እየፈተሸ ቀጥላል። እንደዚህ ፀሃፊ እምነት መሪ ድርጅቱና መንግስት የማጥራት ስራው በይፋ መቆሙ አውጀው ቋሚ ለሆኑ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ተቋማት ( ስነምግባርና ፀረሙስናና ሌሎችም) እስካላስረከቡ ድረስ ከአሁኑ ውጤቱን በማስመልከት መላምቶች ከማስቀመጥ ይልቅ ሂደቱ ላይ ያሉ ተግዳሮቶችና ተስፋዎች መመልከት ተገቢ ነው።በርግጥ የማጥራት ሂደት የት እንደሚደርስ የገባቸው እጃቸው በተለያየ የሙስና ተግባር እንዳለ የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ሂደቱን ለማጨንገፍ ጨለምተኛ የሆኑ ሃሳቦች ቢዘሩ ሌላ መደበቅያና መሸሸግያ ስሌሌላቸው የሚደንቅ አይደለም። ይሁንና ጉዳዩን በቅርቡ ለሚከታተልና የክራይ ሰብሳቢነት ተግባር ሰንሰለት እንዲበጣጠስ ለሚፈልገው አንባቢ በቅርብ እሰከተካሄደው የክልሉ ካቢኔና የመሪ ድርጅቱ አመራር ግምገማ ድረስ የተወሰደት እርምጃዎች በቅርብ ያለኝን መረጃዎች ላቅርብ።

የክልሉ መንግስት የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ከልማት ሳይነጥል በጉዳዩ ላይ የተጠያቂነት አሰራር (Accountability through public opinion) አውጥቶ ከታች ወደላይ ጉዳዩን መልሶ እየመረመረ በየደራጃው ያለው አመራር ራሱን እንዲመለከት እያደረገ ይገኛል። በሚካሄደው ክትትል መሰረት የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉና ጉድለት ያለባቸው ሴክተሮች በወጣው

መመዘኛ መስፈርት መሠረት ለክልሉ ካቢኔ እየቀረበ ተጠያቂ መሆን ያለባቸው አካላት ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች አሉ።ቀጥለዋልም። ይንን ጉዳይ ብዝርዝር ከመመልከታችን በፊት ግን ጉድለቶቹ፣ የጉድለቶቹ አንድምታና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በቅድሚያ መመልከቱ ተገቢ ነው።

## I. የተለዩ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች በጥናትና በህዝባዊ ኮንፈረንስ ከተነሱት የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች መካከል ጎልተው የሚጠቀሱትና የተወሰዱ መፍትሄዎች

- በፍትህ አካላት
  - ✓ ፍርድ ቤቶች፣ አቃብያን ህጎች፣ ፖሊስ መርማሪዎች
    - ከደላሎችና ጠበቆች ጋር ባላቸው ዝምድና ፍትህ ይጓደላል
    - በትልልቅ ወንጀሎች (ህገ-ወጥ የሰው ደላሎች ኮንትሮባንድ፣ አራጣ አበዳሪዎች፣ ፍቺ በተለይም የሴቶች መብት በተመለከተ፣ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች) ላይ ወንጀል ፈፃሚዎች በቀላሉ በዋስትና እየተለቀቁ ከአገር እንዲጠፉ ይደረጋል። ይህ ደግሞ ከግቦና ወገንተኝነት ያልፀዳ መሆኒን ያመለክታል የሚል በዋነኛነት ይጠቀሳል።
- ችግሩ ለመፍታት የተወሰደ እርምጃ

1) ለለአግባብ ሃብት ያካበቱ ካሉ ፀረ ሙስና በያዘው ጥናት ተካትቶና ተጠናክሮ እንዲታይ
2) የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በጥናትና በህዝብ የቀረቡት ቅሬታዎች አጣርቶ እምነት በታጣባቸው በየደረጃው ያሉ ዳኞች ውሳኔ እንዲያሳልፍ ጉዳዮቹን እየመረመረ ይገኛል።
3) በአቃብያን ህጎችና በፖሊስ መርማሪዎችና የወረዳ አዛገች ላይ የማባረርና ህግ ፊት የማቅረብ ስራ ተሰርቷል። ዝርዝሩ በድምር ከተቀመጠው ጋር ቀጥሎ ቀርቧል።
4) በፖሊስ ሃይል የሚታየው የማገርሸት ችግር ለመፍታት በህዝብ በቀጣይነት እየተገመገመ የሚሄድበት ስርአት ወጥቷል።

- በከተሞች
  - ✓ ነባር ይዞታን መዝረክረክና በተጭበረበረ ሰነድ መሬት መቸብቸብ፤
  - ✓ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ተገልጋዩ ለወራት የሚያንገላታ መሆኑ፤

- ✓ የነዋሪዎች የመኖርያ ቤት ግንባታ ፍላጎት አለመፍታት፤
- ✓ የመሠረተ ልማት ችግሮች (በተለይም የመቀሌ ውሃ ችግር) ይጠቀሳሉ።

*መፍትሄ*

- ✓ የከተሞች የነባር ይዞታ የማጥፋት አሰራር ወጥቶለት ከህዝቡ ጋር መግባባት ተደርሶበታል
- ✓ በወጣው አሰራር መሠረት የማጥራት ስራ እየተጠናቀቀ ይገኛል
- ✓ በተጭበረበረ ሰነድ መሬት የቸበቸቡ በህግ ቁጥጥር ስር ውለው እርምጃ ተወስዶል።
- ✓ የማዘጋጃ ቤት የተዝረከረከ አሰራር ለመቀየር የአደረጃጀት ለውጥ ለማካሄድና በአዲስ የተማረ የሰው ሃይል ለማሟላት የሚያስችል የአዋጅ ረቂቅ ተዘጋጅቷል።
- ✓ የመቀሌ የውሃ እጥረት ለመፍታት የአነስተኛ ግድብ ቀሪ ስራዎች ማፋጠንና የዘላቂ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቱ፡ በተያዘለት ግዜ ገደብ እንዲጀመር ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር ያለው ድርድር በፍጥነት እንዲጨረስ መመሪያ ተሰጥቶበታል።

❖ በገጠር

- ✓ የመሬት ህገ-ወጥ ይዞታ መስፋፋት
- ✓ የሴፍት ኔት እርዳታ ማጭበርበር
- ✓ በርካታ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች
- ✓ የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባር
- ✓ የገጠር ወጣቶች የመስርያ ቦታና የብድር አገልግሎት እጥረት (የመሬት ጥያቄ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።)

*መፍትሄ*

- ✓ ብህገ-ወጥ መንገድ ከተያዘ ከ5,513 ሄክታር መሬት ውስጥ 3,459 ሄክታር መሬት እንዲመለስ ተደርጎ ለወጣቶች እንዲቀርብ እየተደረገ ነው፤
- ✓ ከመንግስት ህብረት ስራ ማህበራት ከተዘረፈው 4 ሚልዮን ብር 1.7 ሚልዮን ብር እንዲመለስ ተደርጓል፤
- ✓ የህዝቡ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች በአምስት አመቱ የልማት እቅድ መካተቱ ሴክተሮች እንዲያረጋግጥና ቅደም ተከተል አውጥተው ከህዝቡ ጋር መግባባት እንዲደርሱበት መመርያ ተሰጥቷል፤

- ✓ የወጣቶች የመስሪያ ቦታ (መሬት) ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል መመርያ በካቢኔ ፀድቋል፤

❖ የግብር አስተዳደር ሪፎርም በተመለከተ የተነሱ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች

- o በቤት ክራይና ሽያጭ ላይ የገቢዎች ባለሙያዎች ግምት እንዲያወጡ በመደረጉ ከባለሙያዎቹ ጋር እየተደራደሩ ፍትሃዊ ያልሆነ የግብር አጣጣል እንዲኖር አድርጋል
- o አሁን ካለው የገበያ ዋጋ አንፃር በቫት ሽያጭ መነሻ ካፒታል ሳይሻሻል በመቆየቱ ኢ.ፍትሃዊ ውድድርን እንዲፈጠር አድርጋል
- o በተለያየ ምክንያት ግብር ሳንከፍል ብንዘገይ ወይም ቢያመልጠን ከፍተኛ የአስተዳደር መቀጮ ይጣብናል፣ ተጨባጭ ማስረጃ አቅርበን ግን ከአንድ አመት በላይ የአስተዳደር መቀጮ አይነሳም በሚል በመመርያ መዘጋቱ ለኪሳራ እየደራገን ነው
- o የይግባኝ ጉባኤ ውስጥ የንግዱ ማህበረሰብ ተሳትፎ በተገቢ ሁኔታ አልተመለሰም? በርካታ መዝገብ ባለባቸው አከባቢዎች ይግባኝ እጅግ ይጋተታል

❖ መፍትሂዎች

- o የአከራይ ተከራይና የቤት ሽያጭ በውልና ማስረጃ በቀረበ ውል መሰረት ግብር እንዲከፈል የሚያስችል መመርያ ወጥቶ ተግባራዊ ሆኗል
- o የቫት ምዝገባ መነሻ ካፒታል በፌደራል መንግስት አዋጅ ለማሻሻል በሂደት ላይ ነው
- o የአስተዳደር መቀጮ ይነሳልኝ ጥያቄ በማናቸውም ግዜ እንዲቀርብ የሚያስችል መመርያ በካቢኔ ወጥቶ ተግባራዊ ሆናል
- o የይግባኝ ጉባኤ ውስጥ የዘርፍ ማህበራት አባላት እንዲሆኑ የሚያደርግ መመርያ በካቢኔ ወጥቶ ተግባራዊ መሆን ጀምራል

- o የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መዝገብ በብዛት በሚታይባቸው አከባቢዎች ከአንድ በላይ ጉባኤ ለመሰየም የሚያስችል መመርያ ወጥቶ ተግባራዊ ሆኗል

## III. ሌሎች የተወሰዱ እርምጃዎች

- o በአጠቃላይ በየደረጃው በተካሄደ የማጥራት ስራ ከ1.1 ሚልዮን በላይ ህዝብ የተሳተፈ ሲሆን 223አመራሮች ጉዳያቸው በህግ እንዲታይ ህዝቡ አስተያየት ሰጥቶባቸዋል።በዚህም መሰረትጨ
    - በ41 ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ከአመራር ቦታቸው ተነስተው ባጠፉት መሰረት ህግ ፊት እንዲቀርቡ ተደርጓል
    - 12 ከፍተኛ አመራሮችና 86 መካከለኛ አመራሮች የተሸጋሸጉ ሲሆን
    - ከዝቅተኛው አመራር ወይም የቀበሌ አመራር 1,790 የተሸጋሸጉ ሲሆን 109ኙ ደግሞ ከነበሩበት አመራር ተነስተው ጉዳያቸው ብህግ እየታየ ነው
    - 46 ሰራተኞች በዲስፕሊን ጉዳያቸው እየታየ ሲሆን፣ ከፍተኛ መሃንዲሶች ጨምሮ 17 የመንግስት ሰራተኞች በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው ህግ ፊት እየታየ ነው

## IV. የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመቅረፍ የተወሰዱ ተጨማሪ እርምጃዎችና ያስገኙት ውጤት

- ህዝቡ የራሱን ሚና ለይቶ ለማወቅና በተደራጀ መንገድ መንቀሳቀስ መልካም አስተዳደር ለማስፈን ያለው ጠቀሜታ ሰፊ ግንዛቤ አግኝቶ በማጥራት ሂደት ጥፋተኞችን አጋልጦ ሰጥታል
- የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች መንግስት ለመፍታት ያደረገው እንቅስቃሴ የተደረሰበት የጋራ መግባባት ከ85 በመቶ በላይ መሆኑ

- የወጡት መመርያዎችና አሰራሮች መተግበር በመጀመራቸው የነባር ይዞታ፣ የገጠር መሬት ወረራ፣ በግብር ስርአቱ የተደረጉ ማሻሻያዎች ችግሮቹ መፍታት በመጀመራቸው የህዝቡ ተሳትፉ በየዘርፉ እንዲጨምር አስችላል

- ህዝቡ የተጀመረው ንቅናቄ እንዳይቋረጥ ቁርጠኛ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ አስችሎታል

ከነዚህ እርምጃዎችና ቀጣይ ሆኖ ያለው በየደረጃው ያለ የመንግስትና የድርጅት አመራርና ሰራተኛ ማጥራት ስራ ጎን ለጎን የተጠያቂነት አሰራር (Accountability through public opinion) ወጥቶ የመልካም አስተዳደር ንቅናቀየው ወደ ሃላ እንዳይመለስ ጥረት እየተደረገ ነው። መመዘኛዎቹም ወቅታዊ ምላሽ ለህዝብ በመስጠት (Rapid Response)፣ የተሰጠው ምላሽ ግልፅና የህዝብ እርካታ መፍጠር ላይ ያለበት ደረጃ ፣ እንደ ተቋም ከህዝብ ጋር ቁመና ቀጣይነት ያለው ግኑኝነት ለመፍጠር የሚያስችለው አሰራር አውጥቶ ወደ ስራ የገባ በሚሉ የሚጠቃለሉ ዝርዝር አሰራሮች ናቸው።ህዝቡም ተስፋ ሰንቆ በተደራጀ አገባብ ልማቱን እከወነ በመልካም አስተዳደር ማስፈን ስራ ላይ እየተሳተፈ ይገኛል። እናም ጨለምተኞች ለማስደሰት ሲባል አለአግባብና በተገቢ መረጃ ሳይደገፍ የሚወሰድ እርምጃ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። በኪራይ ሰብሳቢነት ሰንሰለት ያሉትን በሚገባ ሳይጠራ እርምጃ እንዲወሰድ የሚገፋፉም ጉዳያቸው እግረ መንገድ እንዲታለፍና በላይ በላዩ ማስታጋሻ ያገኘ አስመስለው ለማለፍ ካልሆነ በቀር ጠብ የሚል ህዝባዊ ፋይዳ አይኖረውም። ስለሆነም ህዝቡ፣ መሪ ድርጅቱና መንግስት ተሳስረው የጀመሩት ንቅናቄ ዳር ማድረስ ወሳኝ ነው።

ሰላም